https://t.me/ethiopianlegalbrief



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ/ቁ/221716

ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡-1. አቶ ታረቀኝ ዱላ

21. አቶ ግዛቸው የኔው

2. አቶ ጉዲና ዘውዴ
3. አቶ መኮንን ነጋሳ
4. አቶ ዘውዱ ሽብሩ
5. አቶ ተሾመ ባየ
6. አቶ ጎራው ንጉሴ
7. አቶ መሀመድ ሀሰን
8. አቶ አማረ ፍርዴ
9. አቶ ደሞዜ ጌጡ
10. አቶ አብዮት ባዬ
11. አቶ ስማቸው በላይነህ
12. አቶ ሙሉጌታ ተሾመ
13. አቶ ደጀኔ ብርሃኑ
14. አቶ ታጠቅ አሻግሬ
15. አቶ አወቀ ማናምኖ
16. አቶ ተስፋዬ ጥበቡ

22. አቶ በሻህ ተ/ማርቆስ
23. አቶ ገበየሁ ቆጭቶ
24. አቶ ሽድንበር ተጫኔ
25. አቶ ቢያድል በልስቲ
26. አቶ ሀብታሙ ገነት
27. አቶ መንግስቱ ፈጠነ
28. አቶ ደመላሽ አደመ
29. አቶ ዳዊት ጌትነት
30. አቶ ሀብቴ ሞላ ማሞ
31. አቶ ፀጋዬ መጩ
32. አቶ በላይ አሻግሬ
33. አቶ ሲሳይ ጋሻው
34. አቶ አዲስ መኮንን
35. አቶ ሙሉቀን አባይ
36. አቶ ሰለሞን መሌ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

17. አቶ ግርማ ፈለቀ
18. አቶ ተሾመ አዲሱ
19. አቶ አለበል ገላዬ
20. አቶ ጌታሁን መኩሪያ
37. አቶ ኪዳኑ አበራ
38. አቶ ሻምበል የስጋት
39. አቶ ዳምጤ አባት
40.አቶአለማየሁበቀለ ከጠበቃ

ጥሩነሽ

ገረመው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን- ነ/ፊ ነፃነት ጥጋቡ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ስራ ዉል መቋረጥ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነዉ፡፡የክርክሩ አመጣጥ ሲታይ የአሁኑ አመልካቾች ከሳሽ በመሆን በአሁኑ ተጠሪ ላይ በቀን 04/12/2012 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት ክስ አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በተለያየ የስራ መደብ ላይ ተቀጥረው በየወሩ ለእያንዳንዳቸው ብር 3600 እየተከፈለን በመስራት ላይ እንዳለን ቀደም ሲል ተጠሪ ድርጅት የስራ ውላችንን በህገወጥ መንገድ በማቋረጥ ከስራ ስላሰናበተን በፍ/ቤት ክስ መስርተን የድርጅቱ ቋሚ ሰራተኞች ስለመሆናችንና ከህግ ውጪ የስራ ውላችንን የተቋረጠ ስለመሆኑ ተጣርቶ የስራ ውሉ ከተቋረጠ ጊዜ ጀምሮ ያለውን ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሰን ተወስኖ በውሳኔው መሰረት ከተፈፀመ በኋላ ተጠሪ መጋቢት ወር 2011 ዓ.ም ደመወዝ ብቻ በመክፈል ህግን በመተላለፍ አመልካቾች በህግ አግባብ መብታችንን ስላስከበርን ወደ ስራ መልሶ ለማሰራት ሲል በሕግ አግባብ የተደረገ የመዋቅር ለውጥ በሌለበት ሁኔታ የአመልካቾች የስራ መደብ ሳይታጠፍና ሳይሰረዝ ከአመልካቾች ጋር ተመሳሳይ ስራ ያላቸውን ሌሎች ሰራተኞች እንዲሰሩ በማድረግ እና በእኛ የስራ መደብ ላይ ደግሞ ሌሎች ሰራተኞችን በመተካት እና የሰራተኞችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮው ሳያሳውቅና ሳይፈቅድለት በአዋጅ 1156/2011 አንቀጽ 17/1/ሸ/ መሰረት ሚኒስትሩ የሚያወጣውን የሰራተኞች ቅነሳ መመሪያ መሰረት ያላደረገና የአዋጁ አንቀጽ 29 የቅነሳ ቅደም ተከተል ሳይከተል እና የሚገባን ክፍያ ሳይከፍለን የመዋቅር ለውጥና የሰራተኞች ቅነሳ አድርጌአለሁ በማለት ከህግ ውጪ ከስራ ያሰናበተን በመሆኑ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተቋረጠውን ደመወዛችን በመክፈል ወደ ስራችን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲመልሰን፣ ወደ ስራችን የማይመልሰን ከሆነ ከህግ ወጥ የስራ ስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎች እና የስራ ልምድ እንዲወሰንል በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበው መልስ የአመልካቾች የስራ ውል የተቋረጠው በፌዴራል መንግስት የበላይ አመራር በተሾሙ የድርጅቱ ቦርድ በቀን 25/09/2020 ዓ.ም በቃለ-ጉባኤ እና ከፍተኛ የስራ አመራር አባላት ማኔጅመንት በ23/02/2011 ዓ.ም ቃለ-ጉባኤ ባሳለፏቸው ውሳኔዎች ተጠሪ አዲስ አሰራር በመከተል የድርጅቱን ምርታማነት ለማሻሻል የአሰራር ዘዴዎቹን በመለወጡ ምክንያት በድርጅቱ ውስጥ በቀን ሰራተኞች ሲሰሩ የነበሩ የዲስትሪብውሽንና ግንባታ ስራዎች እንዲቆም እና ለ3ኛ ወገን በውል ኮንትራት በመስጠት እንዲሰሩ በሚል በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ተጠሪ ሚያዝያ 01 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ውሳኔውን ተግባራዊ አድርጓል፤ በዚሁ መሰረት በአዋጁ አንቀጽ 28(3)(ሐ) መሰረት ያላቸው የትምህርት ዝግጅት ተጣርቶ የስራ መደቡ የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟሉ ክፍት ቦታዎች ላይ በቋሚነት እንዲቀጠሩ በተባለው መሰረት ተቀጥረዋል፣መስፈርቱን የማያሟሉ የቀን ሰራተኞች ደግሞ በማህበር ተደራጅተው ሲቀርቡ ከሌሎች ማህበራት ቅድሚያ ሥራው በውል እንደሚሰጣቸው በተወሰነው መሰረት የስራ ውላቸው የተቋረጠ በመሆኑ ከቅነሳ ጋር አይገናኝም፤ በአመልካቾች ቦታ የተተካ ሰራተኛ የለም፤ ስለዚህ የአመልካቾች ስራ ለ3ኛ ወገን በቁርጥ ዋጋ በውል በመስጠት (out source) የተደረገ በመሆኑ ወደ ስራ ሊመለሱ አይችሉም፤ ስንብቱ ህጋዊ በመሆኑ የሚከፈላቸው የስንብት ክፍያ እና የካሳ ክፍያ የለም፤ማስጠንቀቂያ ተሰጥታቸዋል፤የዓመት እረፍት በይርጋ ይታገዳል ወይም የቀን ሰራተኞች በመሆናቸዉ የሚከፈላቸው አይኖርም፤የዘገየ ክፍያ በተመለከተ ተጠሪ ያመነው ክፍያ ባለመኖሩ የሚከፈል የዘገየ ክፍያ የለም፤ክሱ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በአዋጁ አንቀጽ 28(3)(ሐ) መሰረት አንድ ድርጅት ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የአሰራር ለውጥ ማድረግ እንደሚቻል፤ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 22275 ላይም (out sourcing) ህጋዊ መሆኑ ተገልጸዋል፤ ስለዚህ በቦርዱ ውሳኔ መሰረት አመልካቾች ሲሰሩ የነበሩ ስራዎችን ለ3ኛ ወገን በቁርጥ ዋጋ በውል በመስጠት ማሰራት መጀመሩ ህጋዊ ተግባር ነው፣ ተጠሪም አመልካቾችን ከስራ ያሰናበተው በህጉ አግባብ ነው በማለት ፍርድ ሲሰጥ ይህ ተግባር ደግሞ ቅናሳ ሳይሆን በማስጠንቀቂያ የስራ ውል መቋረጥ እንደሆነ በሰ/መ/ቁ 38435 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቷል፤ስለዚህ የቅነሳ ሂደት ሊከተለው አይገባም፤አመልካቾች የተሰናበቱት በህጉ አግባብ በመሆኑ ወደ ስራ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሊመለሱ አይገባም፤የስራ ስንብት ክፍያ እና የካሳ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም፤የአመት እረፍት በተመለከተ አመልካቾች የዓመት እረፍት የመጠየቅ መብት ያላቸው ቢሆንም አመልካቾች የዓመት እረፍት እንዲሰጣቸው እየጠየቁ ያለው ስራ ላይ ላልነበሩበት ጊዜ ጨምሮ በመሆኑ እና የህጉ ዓላማ ይህ ባለመሆኑ የአመልካቾች የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ይከፈለን ሲሉ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ተጠሪ የስራ ውል እንደሚቋረጥ ማስታወቂያ ተሰጥቷል በማለት የገለጸ ሲሆን ይህ ማስጠንቀቂያ ሊባል የሚችል ባለመሆኑ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ ለእያንዳንዳቸው የ2 ወር ደመወዝ ብር 7200 እንዲከፈላቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የዘገየ ክፍያ በተመለከተ ተጠሪ አመልካቾችን ከስራ ከማሰናበቱ በፊት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ወይም ጊዜውን የሚተካ ገንዘብ ከፍሎ ሊያሰናበት ሲገባው ይህንን ባለማድረጉ ክፍያ ለዘገየበት የአንድ ወር ደመወዛቸው ለእያንዳንዳቸው ብር 3600 እንዲከፈላቸው እና የስራ ልምድ እንዲሰጣቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 250673 ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መዝገቡን መርምሮ የዘገየው ክፍያ በተመለከተ ተጠሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለአመልካቾች እንዲከፈላቸው የተወሰነው በፍርድ ቤት ነው፤በአንቀጽ 37 መሰረት ሰራተኛው የጠየቀውን ክፍያ አስመልክቶ አለመግባባት የተፈጠረ ከሆነ አሰሪው በአንቀጽ 36 ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሰራተኛው ያመነውን ያህል መክፈል የሚኖርበት ስለመሆኑና በዚህ ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ክፍያ በፍ/ቤት ውሳኔ እንዲከፈል ተብሎ እያለ ይህንን ክፍያ ተጠሪ ለአመልካቾች አስቀድመው ሊከፍል ይገባ ነበር በማለት የስር ፍ/ቤት ክፍያ ዘግይቷል በማለት ቅጣት እንዲከፍል መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት በዚህ ጉዳይ የተወሰነውን በመሻር በሌሎቹ ላይ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ለሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡አመልካቾች የዘገየው ክፍያ ቅጣት ላይ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለተፈጸመበት እንዲታረምልን በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡የአቤቱታ ይዘትም፡- ተጠሪ ያመንኩት እዳ በሌለበት ለዘገየው ክፍያ ቅጣት ሊከፍል አይገባም በማለት በስር ፍ/ቤት በጽሁፍም ሆነ በቃል ምንም አይነት መከራከሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አዲስ ክርክር አቅርቦ በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ማስጠንቀቂያ አለመስጠቱን አምኖ የተከራከረበትና በምስክሮቹ ጭምር የተረጋገጠውን የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በ7 ቀን ውስጥ

ባለመክፈሉ ክፍያ ለዘገየው የ1 ወር ደመወዝ እንዲከፈል በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክፍያው እንዲከፈል የተወሰነው በፍ/ቤት ውሳኔ በመሆኑ የዘገየው ክፍያ ቅጣት ሊከፈለው አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ የሻረበት ሁኔታ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻር በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ክፍያው በፍ/ቤት የተወሰነ ስለሆነ የዘገየበት ክፍያ ሊወሰን አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሻረበት አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 36 እና 38 አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ አመልካቾች ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ስለማስጠንቀቂያ እና የዘገየው ክፍያ ክርክር አላቀረበም፤አምኖ ነው የተከራከረ የሚለው ከእውነት የራቀ ነው፤ ምክንያቱም ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረበው መልስ አመልካቾች የተሰናበቱት በህጋዊ መንገድ በማስታወቂያ ቦርድ ላይ የተለጠፈ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም፤ ያመንኩትና ያዘገየሁት ክፍያ ስለሌለ ክፍያ ለዘገየበት ሊከፍል አይገባም በማለት ሲንከራከር ቆይተን የስር ፍ/ቤት ማስጠንቀቂያ በአግባቡ አልተሰጣቸውም በማለት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈላቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የስር ፍ/ቤት ለዘገየ ክፍያ በተመለከተ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ በተለያዩ መንገድ በስብሰባ አዳራሽ እና በማስታወቂያ ሰሌዳ አሳውቀያለሁ ማስጠንቀቂያ ሊከፍል አይገባም ብሎ እየተከራከረ እያለ አስቀድሞ የማስጠንቀቂያ ክፍያ መክፈል ነበረበት፣ ስለዚህ ሳይከፍል ስለቀረ የ1 ወር ደመወዝ ተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መታረሙ ትክክልኛ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል የነበረዉ የስራ ዉል ግንኙነት የተቋረጠዉ ከህግ ዉጭ ነዉ በማለት አመልካች ያቀረቡትን ዳኝነት ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት መርምሮ ዉሉ የተቋረጠዉ አመልካቾች የተሰማሩበት ስራ በቁርጥ ለሶስተኛ ወገን (out sourcing) እንዲተላላፍ በመወሰኑ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ያረጋገጠዉ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡በአማራጭ ከጠየቁት ልዩ ልዩ ክፍያዎች ዉስጥ አንዱና እዚህ ችሎት

ድረስ ያከራከረዉ የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ክፍያ የዘገየበት ቅጣት የሚመለከተዉ ክፍል ነዉ፡፡

የስራ ዉል በተለያዩ ምክንያቶች ሲቋረጥ አሰሪዉ ደመወዝ እና ከዉሉ መቋረጥ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት የሥራ ቀናት ዉስጥ መከፈል እንዳለበት የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በአስገዳጅ ሁኔታ ደንግጓል፡፡የክፍያዉ ጊዜ ሊራዘም የሚችለዉ ሰራተኛዉ ከአሰሪዉ የተረከበዉን ንብረት በማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማናቸዉም ሂሳብ በማወራረድ ረገድ በራሱ ጥፋት ያዘገየ እንደሆነ ነዉ፡፡(አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 36 ይመለከቷል)፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሰራተኛዉ የጠየቀዉ ክፍያ አከራካሪ ከሆነ አሰሪው ያመነውን ያህል በህጉ በተገለጸዉ ጊዜ ገድብ ዉስጥ መክፈል እንዳለበት የአዋጁ በአንቀጽ 37 ያመለክታል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለዉ የክፍያዉ ዓይነትና መጠን እንደጉዳዩ ባህርይ የሚለያይ በመሆኑ አከራካሪ የሆነዉን እና አከራካሪ ያልሆነዉን በመለየት አሰሪዉ በህግ የተጣለበትን ግዴታ መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡ከአሰሪዉ ቁጥጥር ወጪ የሆነ ምክንያት ሳይኖር ወይም በአንቀጽ 37 ስር በተደነገገው መሰረት የሚያከራክር ክፍያ በሌለበት ሁኔታ ከቅን ልቦና ወጪ ሰራተኛውን ለመጉዳት ተነሳስቶ ክፍያውን ማዘግየቱ ሲረጋገጥ አሰሪው እስከ 3ወር የሚደርስ የሰራተኛውን ደመወዝ ያህል ቅጣት እንዲከፍል የሚገደድ ስለመሆኑ አዋጁ አንቀጽ 38 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት በተመሳሳይ ክርክር በተለያዩ መዝገቦች የሰጠዉ ዉሳኔ አሰሪዉ ክፍያ በማዘግየቱ የማይቀጣዉ የክፍያዉ ራሱ አከራካሪ ሆኖ ሲገኝ መሆኑን አመላክቷል፡፡(በመ/ቁ/74636 እና 67382 ቅጽ 13 ላይ እንደታተመዉ ይመለከታል)፡፡ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ አሰሪዉ ቅጣት እንዲከፍል የሚገደደዉ አከራካሪ ያልሆነ ክፍያ እያለ ያለበቂ ምክንያት ማዘግየቱ ሲረጋገጥ መሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቾች ከጠየቁት ልዩ ልዩ ክፍያዎች ዉስጥ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተወሰነላቸዉ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብቻ ሲሆን ይህንኑ በጊዜ ባለመክፈሉ ቅጣት የአንድ ወር ደመወዝ ለእያንዳንዳቸዉ እንዲከፍል ወስኗል፡፡በዚህ ላይ ተጠሪ ባቀረበዉ ይግባኝ ክርክሩን የመረመረዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ማስታወቂያ መለጠፉን ገልጾ ቢከራከርም በህጉ የተዘረጋዉን ስርዓት ተከትሎ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን አላስረዳም በሚል የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ መሆኑን ነገር ግን ይህ አከራካሪ ክፍያ በፍርድ የተወሰነ በመሆኑ ለዚህ ቅጣት ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማረሙን የዉሳኔዉ ይዘት ያሣያል፡፡አመልካቾች ይህ የቅጣት ገንዘብ መሻሩ ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከሩት በአንድ በኩል ተጠሪ ማስጠንቀቂያ አለመስጠቱን አምኗል በሚል ሲሆን በሌላ በኩል ቅጣት አልከፍልም ብሎ በስር ፍርድ ቤት አልተከራከረም በማለት ነዉ፡፡

መዝገቡ እንደሚያሳዉ ተጠሪ የአመልካቾችን የስራ ዉል ከማቋረጡ በፊት ማስታወቂያ በስራ ቦታ መለጠፉን ገልጸ መከራከሩ ሲታይ ማስጠንቀቂያ አለመስጠቱን አምኗል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ፍርድ ቤቱም የተጠሪን ክርክር ዉድቅ ያደረገዉ ተጠሪ ለጥፋያለሁ የሚለዉ ማስታወቂያ ስለማስጠንቀቂያ አሰጣጥ በአሰሪና ሰራተኛ ህግ የተደነገገዉን ስርዓት የተከተለ አለመሆኑን አረጋግጦ እንጂ ተጠሪ አምኖ በመከራከሩ አለመሆኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡በመሆኑም አመልካች ማስጠንቀቂያ አለመስጠቱን አምኖ ተከራክሯል የሚለዉ የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በሌላ በኩል ቅጣት አስመልክቶ ተጠሪ ክርክሩን ያነሳዉ በይግባኝ ሰሚ ችሎት ነዉ የሚለዉ ቅሬታ ነጥብ በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከራከረዉ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ በማለት ስለመሆኑና በአማራጭ የሚከፈል ክፍያም የለም የሚል አጠቃላይ ክርክር ያነሳ መሆኑን መዝገቡ ስለሚያሣይ ቅጣት ክፍያ ላይ አልተከራከረም የሚያሰኝ አይደለም፡፡ከዚህ ባሻገር ቅጣት እንዳይከፍል በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተወሰነዉ ተጠሪ ያመነዉ ወይም ያለአግባብ የዘገየ ክፍያ አለመኖሩ አረጋግጦ ስለሆነ በዚህ ረገድ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፍል የተወሰነዉ ተጠሪ ለአመልካቾች ማስጠንቀቂያ አለመስጠቱ በክርክር ሂደት በፍርድ ቤቱ ተረጋግጦ በመሆኑ ይህንኑ ክፍያ ያለአግባብ አዘገየ ተብሎ ተጠሪ የሚቀጣበት አግባብ ስሌለለ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቅጣት ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የህጉን ይዘትና ዓላማ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10(1) ድንጋጌዎች መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ በዉሳኔዉ ላይ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማሻሻል መ/ቁጥር 250673 ላይ በቀን 04/05/2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህግ ቁ/ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም